ኢ.ሕ.ባ.ማ
ELA

# ተሚጋች

በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የሚዘጋጅ

# TEMUAGACH

8ኛ ዓመት ቁጥር 1 ጥቅምት 2008

## ርዕሰ አንቀጽ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የተመሠረተ ተበትን 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዩቤልዮ እያከበረ ሲሆን፣ በዓሉን በተመለከተ ከቀረቡት ዝግጅቶች አንዱ "የሕግ ሙያ ማኅበራትና የጥብቅና ድርጅቶች ለሕግ የበላይነትና ለፍትሕ" በሚል ርዕስ ሐምሌ 24 እና 25 ቀን 2007 ዓ.ም. በደሳለኝ ሆቴል የተካሄደው የ2 ቀናት ኮንፍረንስ ነው፡፡ ማኅበሩ በቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ በመመሥረት 12 የአቋም መግለጫ ሃሳቦችን ያወጣ ሲሆን በተለይ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በተቻለ መጠን መቀነስ የሌለበት መሆኑ እና ፍርድ ቤቶችም በግልፅ ሕግ ካልተከለከሉ በስተቀር ዳኝነት አናይም በማለት ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነታቸውን አንወጣም ሊሉ እንደማይገባ የተቀመጠው ሊሠመርበት የሚገባ ነጥብ ነው፡፡ ሕግ የበላይ የሚሆነው ሁሉም ግለሰቦች እና መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ሕግን አክብረው ሲንቀሳቀሱ እና ሕጉን ተላልፈው ከተገኙም በነፃ ፍ/ቤት ተከሰው በገለልተኛ ዳኛ ዳኝነት ታይቶ ሕጉን እንዲያከብሩ የሚገደዱ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

ስለሕግ የበላይነት ስናነሳ መረሳት የሌለበት ሕግ በዜጐችና በመንግሥት ወይም በባለሥልጣናቱ መካከል ብቻ ሳይሆን በዜጐች የእርስ በእርስ የግል ግንኙነቶች ውስጥም በእኩልነት መፈፀም ያለበት መሆኑንም ነው፡፡ ዜጐች በንግድ በሥራም ሆነ በግል ግንኙነታቸው ወይም ከመንግሥት ጋር ባላቸው ግንኙነት ሕግን ሊያከብሩ የሚችሉት ስለ ሕጉ መረጃ ካላቸው ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአንዳንድ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕግ በተለይ በሀገሪቱ ርዕሰ መዲና በአዲስ አበባ እንደልብ የማይገኝ መሆኑ እና ቋሚ ማከፋፈያ እና መሸጫ ቦታ አለመኖሩ አሳሳቢ ነው፡፡ ለነገሩ የአዲስ አበባ መስተዳድር ሕጐችም በቀላሉ አይገኙም፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት እራሱ ስለሚያስፈጽመው ሕጐች ለሕዝቡም ሆነ ለየሚመለከታቸው ሰዎች (ሴክተሮች) መሠረታዊ ግንዛቤ ማስጨባጫ በቀጣይነት መስጠት አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በየጊዜው ስለ ግብር እና ታክስ ሕጐች በሚዲያ የሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ በአርአያነቱ ተጠቃሽ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ፍ/ቤቶች፣ የፍትሕ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርን ጨምሮ ልዩ ልዩ የሕግ ሙያ ማኅበራት ተባብረው መሥራት ኅብረተሰቡ ሕጉን እንዲያውቅ እና እንዲተገብር ሚዲያን በመጠቀም በልዩ ልዩ ዘዴዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሥራት አለባቸው፡፡

በመጨረሻም በአሁኑ ጊዜ የሀገራችን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ሲሆን በአንድ ሰው ላይ የተመሠረተው የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ ኋላቀር እና ከኢኮኖሚው ጋር እኩል መጓዝ አለመቻሉ መታወቅ አለበት፡፡ እንደሌሎች ሀገሮች የጥብቅና ድርጅቶች (ፈርሞች) ተቋቁመው በቡድን አገልግሎት ወደ መስጠት መሸጋገር የግድ ይላል፡፡ በዚህ ረገድ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ አዋጅ ቁ. 199/1992 ዓ.ም. የሕግ ፈርሞች (የጥብቅና ድርጅቶች) እንደሚቋቋሙ ቢገልጽም ዝርዝር ደንብ (መመሪያ) ባለመውጣቱ አልተተገበረም፡፡ ስለዚህም የፈርም ሕግ በቶሎ ወጥቶ የጥብቅና ድርጅቶች ተቋቁመው ሙያው የኢንቨስተሩን ፍላጐት ወደሚያረካ የአገልግሎት አሰጣጥ ሊሸጋገር ይገባል፡፡ በሌላ በኩልም የዳኝነት አሠጣጥ እና የፍትሕ ሴክተሩ ኢኮኖሚው እየተጓዘ ባለበት ፍጥነት አብሮ ለመጓዝ ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት መስጠት ያለበት ሲሆን፣ በሰው ኃይልም ሆነ በገንዘብና በማቴሪያል ዐቅሙ ሊጠናከር ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ የፍትሕ ዘርፉ በአጠቃላይ ሥራውን ገለልተኛ እና ከሙስናና ልዩ ልዩ አድልዎ በፀዳ ሁኔታ መሥራቱን መቆጣጠር የሚቻልበት ሥርዓት መኖር አለበት፡፡ እንዲሁም የሕግ ሙያ እንዲያድግ፣ ኅብረተሰቡም ሆነ ኢኮኖሚው የሚጠብቁትን ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲያገኙ ከተፈለገ የሙያ ማኅበሩ በአዋጅ ሊቋቋም እና መንግሥት ማኅበሩን ባሳተፈ ሁኔታ የጥብቅና ፈቃድ የሚሰጥበት፣ እንዲሁም ማኅበሩ የሥነ ምግባር ደንብ የሚያወጣበት፣ ሥነ ምግባር በሚጥሱ ባለሙያዎች ላይ እርምጃ የሚወስድበትና ባአጠቃላይ ማኅበሩ እንደሌሎቹ ሀገሮች ሙያውን የሚያሳድግበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል፡፡■

## ለአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ በብሔራዊ ቤተመንግሥት በተደረገላቸው የራት ግብዣ ላይ ከተጠሩት መካከል ማኅበሩ ይገኝበታል

ባራክ ሁሴን ኦባማ ሀገራችንን በሥልጣን ላይ ሆነው የጐበኙ የመጀመሪያው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኃይለማርያም ደሳለኝ ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ.ም. በብሔራዊ ቤተመንግሥት ለፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ባደረጉላቸው የራት ግብዣ ታዋቂ ሰዎችን ጨምሮ 300 የሚሆኑ ሰዎች መጠራታቸው ይታወሳል፡፡ ከእነኝህም መካከል የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ይገኙበታል፡፡ አንዳንድ ባለሙያዎች መንግሥት ለማኅበሩ እና ለሲቪክ ማኅበራት የሚሰጠው ትኩረት እየ ጨመረ መምጣቱን ያሳያል ብለዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዘንድሮ የዓለም አቀፍ የሲቪክ ማኅበራት ቀን

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በሀዋሳ ከተማ የግማሽ ቀን አውደ ጥናት አካሄደ ነፃ የሕግ አገልግሎት መስጫ ማዕከሉ ተጐበኘ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ ከተማ ሀዋሳ ቅዳሜ መስከረም 22 ቀን 2008 ዓ.ም. የግማሽ ቀን አውደ ጥናት አካሄደ፡፡ አውደ ጥናቱ የተካሄደው ጠበቆች በክልሉ ፍ/ቤት ዙሪያ ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮች፣ በክልሉ ፍ/ቤቶች አሠራር ዙሪያ እና ስለጠበቆች ሥነ-ምግባር ሲሆን፣ አቶ ሠመረ አሰፋ (በፌደራል ፍ/ቤቶች እና በደቡብ ክልል ፍ/ቤቶች የሕግ አማካሪና ጠበቃ) እና የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ታምራት ኪዳነ ማርያም ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ በተጨማሪም የደቡብ ክልል የጠበቆች ማኅበር ም/ፕሬዚዳንት አቶ ነጋ ከበደ አማካኝነት በክልሉ በጠበቆች ታክስ አከፋፈል ዙሪያ ስለሚታዩ ችግሮች ገለጻ የቀረበ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አበበ አሳመረ አወያይነት በተነሱት ነጥቦች ተሳታፊው ተነጋግሮባቸዋል፡፡ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የብራዚል የሙስና ሕግ ከፍተኛ ምዝበራን ለማጋለጥና የሕዝብ ገንዘብ ለማስመለስ ረዳ ተባለ

የብራዚል ፌደራል ፖሊስ "ዘመቻ የመኪና እጥበት" ወይም "operation car wash" ብሎ በሰየመው የወንጀል ምርመራ በርካታ ሰዎች ተጋልጠዋል፡፡ እስከ ባለፈው ግንቦት ወር 2007 ዓ.ም. ድረስ በወንጀሉ 315 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በመመዝበሩ የተደረሰበት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 157 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማስመለስ ተችሏል፡፡ በርካታ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች የብራዚሉ

(ወደ ገጽ 5 ዞሯል)

# የአቋም መግለጫ

1. የሕግ ሙያ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. 2025 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመግባት ላላት ዕቅድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ሙያው ለኢኮኖሚው ያለው አስተዋጽኦ ሊጠና ይገባል፡፡
2. የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት የታለመለትን ግብ ለመምታት የሕግ የበላይነት ደረጃ በደረጃ ሊሰፍን ይገባል፡፡ ከዚህም ጋር አብሮ የሕግ አገልግሎት አሰጣጡ ሊሻሻል ይገባል፡፡ በአንድ ሰው አገልግሎት ከመስጠት በቡድን አገልግሎት ወደ መስጠት የሚሸጋገርበት መንገድ መፈለግ አለበት፡፡
3. የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የኢትዮጵያ የሕግ/ጥብቅና አገልግሎት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እያበረከተ ያለውን እና ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ ሊያስጠና ይገባል፡፡
4. የጥብቅና ድርጅቶች/ፈርም/ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻልና ኢኮኖሚውን ለማሳደግ እንደሚጠቅሙ የሚመለከተው የመንግሥት አካል የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ከግምት ውስጥ ሊያስገባው ይገባል፡፡ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ አዋጅ በሚያዘው መሠረት የጥብቅና ድርጅት/ፈርም/ መመሪያ ሊወጣ ይገባል፡፡ የሙያ ማኅበሩ እና ጠበቆች በሙሉ በሕግ አወጣጡ ላይ ሊሳተፉ ይገባል፡፡
5. የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ስለጥብቅና ድርጅቶች አስተዳደር በተከታታይ ዓውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት የጠበቆች ግንዛቤ እንዲጨምር ሊሠራ ይገባል፡፡
6. የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ውሣኔ በተለይም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ተገማች ሊሆን ይገባል፡፡ ማኅበሩ አከራካሪ በሆኑና ተቀባይነት ያለው አቋም ባልተያዘባቸው ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ፣ ትምህርታዊ ውይይቶችን (workshops) እና የምርምር ጽሑፎችን በማቅረብ ፍ/ቤቱን ሊደግፈው ይገባል፡፡
7. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው የሚወጡት ሕጎች ግልጽና ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለምአቀፍ ስምምነቶች የማይጥሱ መሆናቸውን ሊቆጣጠሩ ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርም በሕግ ማርቀቅ ላይ ሊሳተፍ ይገባል፡፡
8. ማኅበሩ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሕግ የበላይነት ዕውቀት እንዲጨምር መሥራት አለበት፡፡ ኢ.ሕ.ባ.ማ (ELA) ከፍርድ ቤቶችና ከፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር መሠረታዊ የሕግ ዕውቀት በሕዝቡ እንዲሠርጽ መሥራት አለበት፡፡ በየዘርፉ የሚመለከታቸው ሰዎች ተገቢውን ዕውቀት እንዲያገኙ መሠራት አለበት፡፡
9. የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 በሚያዘው መሠረት በተቻለ መጠን የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን መነጠቅ የለበትም፡፡ ፍ/ቤቶች ሕግ ዳኝነት እንዳይሰጡ በግልጽ ካልከለከላቸው በስተቀር ዳኝነት አንሰጥም(አናይም) እያሉ መዝገቦችን መዝጋት የለባቸውም፡፡
10. አንጋፋው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በአዋጅ መልክ ሊቋቋም ይገባል፡፡ ሁሉም ጠበቃ የሙያ ማኅበሩ አባል እንዲሆን ሊገደድ ይገባል፡፡ የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴርም እያንዳንዱ ጠበቃ የሙያ ማኅበሩ አባል እንዲሆን፣ በማኅበሩ የሚዘጋጁትን ትምህርታዊ ውይይቶች እንዲካፈል፣ የአባልነት ክፍያ ግዴታውን እንዲወጣ ሊያበረታታ ይገባል፡፡
11. በማኅበራት መካከል ትብብር መኖር አለበት፡፡
12. የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር መንግሥትን ባሳተፈ ሁኔታ ሙያውን እንዲቆጣጠር የሥነ-ምግባር ደንብ እንዲያወጣ፣ ዲሲፕሊን ሲጣስ እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ አለበት፡፡ ሙያ ማኅበሩም ሆነ አባሉ እንዲሁም ጠበቆች በንቃት በመሣተፍ ለዚህ ብቁ መሆኑን ማስመስከር አለበት፡፡ የሚመለከተው አካልም እንዲያምንበት ቀጣይነት ያላቸው ውይይቶችና አውደጥናቶች በማኅበሩ መዘጋጀት አለባቸው፡፡■

## ለአሜሪካው ፕሬዚዳንት... (ከገጽ 1 የዞረ)

መስከረም 4 ቀን 2008 ዓ.ም. “Space for Civic Societies” “ለሲቪክ ማኅበራት ዕድል ይሰጣቸው” በሚል መሪ ቃል እንዲከበር በማዘዙ በዓሉ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተከብሯል፡፡ በዕለቱ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ እሸቱ ገብሬ ስለዲሞክራሲ እና ስለሲቪክ ማኅበራት ሚና በፓርላማው አዳራሽ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበው ሰፊ ውይይት ተደርጐበታል፡፡ በዓውደ ጥናቱ ላይ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርን ጨምሮ ልዩ ልዩ የሲቪክ ማኅበራት እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ተሳትፈውበታል፡፡■

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር አምባሳደር፣ ኪዳኔ በየነ ሕንፃ፣ 1ኛ ፎቅ በሚገኘው ጽ/ቤቱ ውስጥ ባደራጀው ቤተ መጻሕፍታችን (የመረጃ ማዕከል) ይጠቀሙ፡፡ አባላት ዌብሳይታችንን በመጠቀም የጥብቅና አገልግሎታቸውን ማስተዋወቅ ይችላሉ፡፡

የማኅበሩ ጽ/ቤት

ወቅታዊ ጉዳይ

# የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የተመሠረተበትን 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዩ በዓል በልዩ ልዩ ዝግጅቶች አከበረ፤ ማኅበሩ በ1957 ዓ.ም. ተቋቁሞ በ1958 ዓ.ም. በመንግሥት እንደመመዝገቡ ክብረበዓሉም በ2008 ዓ.ም. በልዩ ልዩ ዝግጅቶች እንደሚከበር ታውቋል

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በ1957 ዓ.ም. በተወሰኑ ጠበቆች አነሳሽነት በእድር መልክ ተቋቋመ፡፡ ማኅበሩ በ1958 ዓ.ም. በወቅቱ በነበረው የአገር ግዛት ሚኒስቴር የጠበቆች ማኅበር በሚል ስያሜ በሙያ ማኅበርነት ተመዝግቧል፡፡ ከዚያም በ1967 ዓ.ም. የስም ለውጥ በማድረግ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ተብሎ ተጠርቷል፡፡ በመቀጠልም በ1997 ዓ.ም. የመተዳደሪያ ደንቡ ተሻሽሎ የኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር (Ethiopian Bar Association) በሚል ስያሜ ሲጠራ ቆይቷል፡፡ በአዋጅ ቁ. 621/2001 ዓ.ም. መሠረት ማኅበራት እንደገና እንዲመዘገቡ ሲደረግ ማኅበሩ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር (The Ethiopian Lawyers' Association) በሚል ስያሜ ተመዝግቦ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

የማኅበሩን ያለፉትን ዓመታት እንቅስቃሴዎች ስንገመግም ምንም እንኳን ያሳለፈውን ረዥም ዘመን የሚመጥን ሥራ አለመሥራቱ ባይካድም አገራችን የመደራጀት እና ሃሣብን የመግለጽ ነፃነትን እምብዛም በማያበረታታው የሶሻሊዝም ሥርዓት በርካታ ዓመታትን ማሳለፏን እና በዲሞክራሲ ጀማሪዎች መሆናችንን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል፡፡

ማኅበሩ ለበርካታ ዓመታት በፍትሕ ሚኒስቴር የጠበቆች የሥነ ምግባር ኮሚቴ (ቦርድ) ውስጥ በመሳተፍ ባለሙያው የሙያውን ደንብና ሥነ-ምግባር አክብሮ እንዲሠራ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ማኅበሩ በተላልቅ አገራዊ ጉዳዮች በመሳተፍ ለሀገር፣ ለሕዝብና ለመንግሥት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በየጊዜው በአሳሳቢ አከራካሪና ውስብስብ የሕግ ጉዳዮች በርካታ አውደ ጥናቶችንና ትምህርታዊ ውይይቶችን በማዘጋጀት የባለሙያውን የሕግ ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ የሕግና የአሠራር ክፍተቶችን በማመላከት ሕጐች እንዲሻሻሉ እና አዳዲስ ሕጐች እንዲወጡ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ረቂቅ ሕጐችን በሚመለከት ሲ.ጋበዝ ሃሣብ በመስጠት በሕግ አወጣጥ ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከ1998 ዓ.ም. ወዲህ በዓመት 2 ጊዜ የሚወጣ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔትን በማሳተም የሀገሪቱ ሥነ ሕግ (ጁሪስፕሩደንስ) እንዲዳብር የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

ማኅበሩ ምንም እንኳን መዋጮአቸውን በወቅቱ የመክፈል እና በስብሰባ ተሚልቶ የመገኘት ችግር ቢኖርም 700 የሚሆኑ አባላት አሉት፡፡

ከ50ኛው ዓመት ክብረበዓል ጋር በተያያዘ፡- 1ኛ/ ሐምሌ 16 ቀን 2007 ዓ.ም. በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ ወጥ አቋም ካልተያዘባቸው እና በአሁኑ ጊዜ በጣም አከራካሪ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የወራሽነት መብት በይርጋ ሊታገድ ስለሚችልበት እና ስለማይችልበት የግንዛቤ ማስጨበጫ ችሎት ተዘጋጅቶ ግንዛቤን የሚያጐለብቱ ክርክሮች ተደርገው ትምህርታዊ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡ በክርክሩ ውስጥ በአንድ በኩል ወ/ሮ አበባ መንግሥቱ እና አቶ ዮሴፍ አዕምሮ በሌላ በኩል ደግሞ አቶ አሰፋ ዓሊ እና አቶ ተስፋዬ ደረሰ (ሁሉም የሕግ አማካሪና ጠበቆች) በጠበቃነት ተከራክረዋል፡፡ አቶ ፊልጶስ አይናለም አሚከስ ኩሪያ "ሃሳብ አቅራቢ"

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር...

(ከገጽ 1 የዞረ)

በመጨረሻም አቶ ፈቃዱ ደምሴ በኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር የጠበቆች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አማካ ኝነት ፍትሕ ሚኒስቴርን በሚመ ለከት ለተነሱት ጥያቄዎች ማብራሪያ ተሰጥ ቶባቸው ስብሰባው ተጠናቋል፡፡ በስብ ሰባው ከ45 በላይ ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን፣ ግማሾቹ ዳኞች፣ ዐቃቤ ሕጎችና ከተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተወክለው የመጡ የሕግ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ የማኅበሩ አባል ለመሆን ለሚፈልጉ ሰዎች ፎርም ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በክልሉ የማኅበሩን ሥራ ለማስተባበር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች ስማቸውን ሰጥተዋል፡፡

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከኢትዮጵያ ወጣት የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ጋር በመተባበር የሚያስተዳድረው የነፃ የሕግ አገልግሎት መስጫ ማዕከል በዕለቱ ተጐብኝቷል፡፡ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለማዕከሉ ደረጃውን የጠበቀ ቢሮ መስጠቱ የሚያስመሰግን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አገልግሎቱ የሚያስፈልጋቸው ብዙ ሰዎች የሚገኙት በወረዳና በዞን ፍ/ቤቶች ነው፡፡ ስለዚህ ማዕከሉ እራሱን ለማስተዋወቅ ወይም ሌላ ተጨማሪ ቢሮ ለማግኘት መሞከር እንዳለበት ገለጻ ተደርጓል፡፡ በሀዋሳ ዙሪያ የሚገኙ የነፃ የሕግ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት እርስ በእርስ ተቀናጅተው መሥራት እንዳለባቸው ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በቀጣይም የማኅበሩ አመራር በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ማዕከላትንም እየጎበኘ ችግሮቻቸውን ለመረዳትና ለመፍታት ጥረት ይደረጋል፡፡■

**ተሚጋች** - በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በየሁለት ወር የሚታተም

ስልክ : 251-11-553-01-22
ፖ.ሣ.ቁ. : 700
ፋክስ : 251-11-515-20-47
አዲስ አበባ : ኢትዮጵያ
ኢ-ሜይል : eba@ethionet.et
ዌብሳይት : www.ethiopian-bar.org

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የተመሠረተበትን... ከገጽ 3 የዞረ

በመሆን በጥናት ላይ የተመሠረተ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡ በዳኝነት አቶ ተስፋዬ ኃይለማርያም (የቀድሞ የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ እና የሕግ አማካሪና ጠበቃ)፣ ወ/ሮ ዜናዬ ታደሰ (የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር)፣ አቶ ቴዎድሮስ ምህረት (የሕግ አማካሪ፣ ጠበቃና በአ.አ.ዩ የሕግና የአስተዳደር ኮሌጅ መምህር)፣ ወ/ሮ ማርታ በለጠ (በአ.አ.ዩ. የሕግና የአስተዳደር ኮሌጅ መምህር) እና አቶ መታሰቢያ ኃይሉ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ) በሙሉ ድምፅ አስተማሪነት ያለው ፍርድ በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡

2ኛ/ ሐምሌ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ከአውሮፓ ኅብረት ሲቪል ሶሳይቲ ፈንድ II በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሚኒስቴር መ/ቤቱ አዳራሽ ስለጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ አጠቃላይ ጥናት በአቶ አብደላ አሊ (የሕግ አማካሪና ጠበቃ)፣ በሌላ በኩል በተግባር ስላለው ተጨባጭ ሁኔታ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጠበቆች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ፈቃዱ ደምሴ አማካኝነት ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቦ በአቶ አበበ አሳመረ (የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት) አወያይነት በበርካታ ነጥቦች ዙሪያ የሙሉ ቀን ትምህርታዊ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በተለይ በአቶ ፈቃዱ ደምሴ በኩል በዲሲፕሊን ጉዳይ ዳኝነት የሚሰጠው አካል የፍትሕ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሳይሆን ከጠበቆች 2፣ ከፍ/ቤት 1 እና ከፍትሕ ሚኒስቴር 2 አባላት በተውጣጣ ኮሚቴ መሆኑን ገልፀው በዳኝነቱ ላይ ቅሬታ ያላቸው ባለሙያዎች የፍትሕ ሚኒስቴር እንደበደላቸው አድርገው መናገር ተገቢ አለመሆኑን አሳስበዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን አንዳንድ ተሳታፊዎች ማኅበሩ እንደቀድሞው በዳኝነቱ ውስጥ እንዲሳተፍ ቢደረግ (ወንበር ቢሰጠው) እና በውሣኔው ላይ የማኅበሩ ተወካይ ቢፈርምበት ፍትሕ ሚኒስቴር ላይ የሚቀርበው ስሞታ ሊቀንስ እንደሚችልና ለመታረምም የተሻለ በር እንደሚከፍት ሃሣብ አቅርበዋል፡፡ በሌላ በኩል አቶ ፈቃዱ ደምሴ በሥራ ላይ ያለው የጥብቅና ፈቃድ አሠጣጥ አዋጁ ሊሻሻል እንደሚችል ገልፀው በዚህ ላይ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ተሳትፎ እንዲያደርግ እንደሚጋበዝ ገልፀዋል፡፡

ተሳታፊዎቹም የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ለእንዲህ ዓይነት አውደ ጥናት አዳራሹን ከመፍቀድ ባለፈ ግልጽነት በተሞላው ሁኔታ በጉዳዩ ላይ ከጠበቆች ጋር መወያየቱ ጥሩ አሠራር መሆኑን አድንቀው ለወደፊቱም ይህ ልምድ ሊቀጥል እንደሚገባ ሃሣብ አቅርበዋል፡፡

3ኛ/ ሌላው ከ50ኛው ዓመት የወርቅ ኢዩቤልዩ ክብረ በዓል ጋር በተያያዘ የተከናወነው የበዓሉ ማስታወሻ መጽሔት ነው፡፡ "ስለጥብቅና ሙያ በኢትዮጵያ፣ ጥንስሱና አነሳሱ" በሚል ርዕስ በ50ኛው ዓመት የመጽሔት ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ታምሩ ወንድማገኝሁ የተዘጋጀ ታሪካዊና አስተማሪ ጽሑፍን ያካተተ ነው፡፡ ማኅበሩም ከተመሠረተ አንስቶ በፕሬዚዳንትነት ያገለገሉ ሰዎች ስምና ፎቶግራፍም አለበት፡፡ ልዩ ተሰጥኦ ካላቸው የሕግ ባለሙያዎች መካከል ከጠበቃና አርቲስት አበበ ባልቻ፣ ከጠበቃና ደራሲ አሳምነው ባረጋ እና ከጠበቃና ድምፃዊ ቴዎድሮስ ሞሲሳ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ይገኝበታል፡፡ በተለይ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 84623 ሰኔ 4 ቀን 2005 ዓ.ም. በአመልካች በእነ ጂ አግሪ ፓክ ኃ.የተ.የግ. ማኅበር እና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሃዋሣ ቅርንጫፍ መካከል አንድ ሰው ገቢውን ለግብር ሰብሳቢው አሳውቆ ነገር ግን ግብር ላለመክፈል ሲል ንብረቱን ካሸሸ በወንጀል ከሚጠየቅ በስተቀር ግብር አስገቢው መሥሪያ ቤት በግምት የወሰነውን ግብር ወይም በሌላ አነጋገር የፍትሐብሔር ዕዳ ለመክፈል አለመቻል ግን በወንጀል ሊያስጠይቅ እንደማይገባ እና ኢትዮጵያ ያጸደቀችውን ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነትና ሕገ-መንግሥቱን እንደሚጥስ በመግለፅ አመልካቾቹን ከወንጀሉ ክስ በነፃ ያሰናበተበት ፍርድ በምርጥ ፍርድነት ተካቷል፡፡ ሌሎችም አስተማሪና አዝናኝ ጽሑፎች ያሉበት ሲሆን፣ በተለይ በአቶ ኤልያስ ተወልደብርሃን (የሕግ አማካሪና ጠበቃ) ስለ ጥብቅና ዋጋ አተማመን እንዲሁም በአቶ ሰሎሞን ጓንጉል (የሕግ አማካሪና ጠበቃ) ሕግና ፍትሕ ሲጣሉ በሚል ርዕስ በ1967 ዓ.ም. (በቀድሞው መንግሥት) የ1955 ዓ.ም. የጡረታ አዋጅ ተሻሽሎ 3 ዓመትና ከዚያ በላይ የታሠረ ሰው የጡረታ መብት እንዲያጣ መደረጉን እና ይህ በ1995 ዓ.ም. በወጣው የጡረታ አዋጅ ቢሻርም የሰበር ፍ/ቤት ቀደም ሲል ጡረታ የወጡ ሰዎችን የ1995 ዓ.ም. ሕግ አይመለከታቸውም ማለቱን አንስተው አስተማሪ ጽሑፍ አበርክተዋል፡፡

በመጽሔት ኮሚቴ አባልነት 1ኛ/ አቶ ታምሩ ወንድማገኝሁ 2ኛ/ አቶ አበባየሁ ለገሠ 3ኛ/ አቶ አብዱልፈታህ አብደላህ እና እና 4ኛ/ ወ/ት ሌንሳ ቢየና (ከጽ/ቤቱ) ጊዜያቸውን በመሰዋት በከፍተኛ ሁኔታ አገልግለዋል፡፡

4ኛ/ የ50ኛው የወርቅ ኢዩቤልዮ ክብረ በዓል 4ኛው ክንዋኔ ሐምሌ 24 እና 25 ቀን 2007 ዓ.ም. "የሕግ ሙያ ማኅበራት እና የጥብቅና ድርጅቶች ለሕግ የበላይነትና ለፍትሕ" በሚል መርህ በደሳለኝ ሆቴል የተከናወነው የ50ኛው ዓመት ልዩ ኮንፈረንስ ነው፡፡ ኮንፈረንሱ ክቡር የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴርን በመወከል የጠበቆች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ፈቃዱ ደምሴ በንግግር ከፍተውታል፡፡ በአጠቃላይ በ6 ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ እነዚህም ሀ/ ዘመናዊው የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ከየት ወደ የት በሚል ርዕስ በአቶ ግርማሥላሴ አርአያ ጽሑፍ አቅራቢነት፣ በአቶ ታምሩ ወንድማገኝሁ አወያይነት ለ/የፍ/ቤቶች ሚና የሕግ የበላይነትን ከማስፈን አኳያ በሚል ርዕስ በተባባሪ ፕሮፌሰር አሰፋ ፍስሐ አቅራቢነት፣ በዶ/ር ጌታቸው አሰፋ አወያይነት

**(ወደ ገጽ 5 ዞሯል)**

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የተመሠረተበትን... ከገጽ 4 የዞረ

ሐ/ ስለሕግ የበላይነት መርሆዎች በአቶ ታምራት ኪዳነማርያም አቅራቢነት፣ በአቶ ጌዴዎን ወልደዮሐንስ አወያይነት መ/ የሕግ ሙያ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ስላለው አስተዋጽኦ [ያደጉ ሀገሮችን (እንግሊዝን) እና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ላይ ያሉ ታዳጊ ሀገሮችን በማገናዘብ የቀረበ ጥናት] በሚል ርዕስ በሚ/ር ሮበርት ሚላርድ (ከዓለም የጠበቆች ማኅበር የመጡ ባለሙያ) አቅራቢነት፣ በአቶ ምህረተዓብ ልዑል አወያይነት፣ ሠ/ የጥብቅና ድርጅቶችን አስተዳደር ማሻሻል ብቃትን ለመጨመርና ኃላፊነትን ለመቀነስ ስለሚኖረው አስተዋጽኦ በሚል ርዕስ በዶ/ር ሄርማን ጄ ኖት(ከዓለም ጠበቆች ማኅበር የመጡ ባለሙያ) አቅራቢነት በአቶ ምህረተዓብ ልዑል አወያይነት እና ረ/ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበራት ሁነት እና የሌሎች ሀገሮች ልምድ በሚል ርዕስ በአቶ ወንድማገኘሁ ገብረሥላሴ አቅራቢነት፣ በአቶ ስሜነህ ኪሮስ አወያይነት ኮንፈረንሱ (ዓውደ ጥናቱ) ተካሂዶ በተሳታፊው ደማቅ ውይይት ተደርጓል፡፡

ኮንፈረንሱ ታሪካዊ መሆኑን በማሰብ በቪዲዮ እንዲቀረጽ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ከዓለም ጠበቆች ማኅበር የመጡት እንግዶች ውይይቱን እንዲከታተሉ በማሰብ ፕሮፌሽናል ተርጓሚ ተቀጥሮ ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ እየተተረጐመ በማዳመጫ ከመከታተላቸውም በላይ በእንግሊዝኛ የቀረቡ ጽሑፎችና ውይይቶችም በአማርኛ እየተተረጐሙ የሚፈልግ በማዳመጫ የሚከታተልበት እና ጥያቄዎች በአማርኛ ቀርበው በእንግሊዝኛ የሚመለሱበትና የሚተረጐሙበት ሁኔታ ስለነበር ውይይቱ በጣም አሳታፊና ስኬታማ በሆነ መንገድ ተካሂዷል፡፡ በመጨረሻም በቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ በመመሥረት ባለ 12 ነጥብ የአቋም መግለጫ ተነቦ ኮንፈረንሱ የተጠናቀቀ ሲሆን የአቋም መግለጫዎቹ የማኅበሩ የወደፊት ዕቅዶችና ሥራዎች ውስጥ ይካተታሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ (የአቋም መግለጫዎቹን ሙሉ ይዘት በገፅ 2 ላይ ይመልከቱ፡፡) በውይይቱ ላይ ከአባላት በተጨማሪ ጥሪ የተደረገላቸው የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤት ተወካዮች ከመገኘታቸውም በላይ በተለይም ከፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ ከሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ፣ ከኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከዩ ኤስ አይ ዲ እና ከአውሮፓ ኅብረት ሲቪል ሶሳይቲ ፈንድ II የመጡ ባለሙያዎችና ተወካዮች ተሳትፈዋል፡፡

5ኛ/ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር 50ኛ ዓመት ክብረ በዓል በ2008 ዓ.ም. በልዩ ልዩ ዝግጅቶች መከበሩ የሚቀጥል ሲሆን በተለይ በፎቶግራፍ እና ዶክመንት ኤግዚቢሽን እንዲሁም ለሀገራችን የሕግ ሙያ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰዎችን በመዘከር የሚከበር ይሆናል፡፡■

## የብራዚል የሙስና ሕግ... ከገጽ 1 የዞረ

የሕዝብ የቤንዚን ኩባንያ ለሚያስገነባቸው የሚሊዮንና ቢሊዮን ሥራዎች ጨረታ ለማሸነፍ በአቀባባዮች በኩል ጉቦ መክፈላቸው ተደርሶበታል፡፡

ወንጀሉ ሊደረስበት የቻለው ኤልቤርቶ ዩሴፍ የተባለ ገንዘብ መንዛሪ ፔትሮብራስ ለተባለው የሕዝብ ኮርፖሬሽን ዳይሬክተር (ፓውሎ ሮቤርቶ ኮስታ) ውድ የቅንጦት መኪና ከውጪ ሀገር አስመጥቶ መስጠቱን መነሻ በማድረግ በተጣራ ምርመራ ነው፡፡ በብራዚል የሙስና ሕግ ዐቃቤ ሕግና ተጠርጣሪው በፍ/ቤት የሚጸድቅ የመተባበር ስምምነት መፈራረም ይችላሉ፡፡ ተጠርጣሪው በወንጀሉ ያገዘውን ሰው ማንነት ለመግለጽ ወይም ቡድኑን ለማጋለጥ ወይም የተመዘበረውን ገንዘብ በሙሉ/በከፊል ለመመለስ ወዘተ እና ዐቃቤ ሕግ ደግሞ ተጠርጣሪው ቅጣት እስከ 2/3ኛ ድረስ እንዲቀነስለት ወይም በእስራት እንዳይቀጣ ወይም ከነአካቴው እንዳይቀጣ ለመስማማት ይችላሉ፡፡ ስምምነቱ ግን የሚፀናው በፍ/ቤት ሲጸድቅ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ገንዘብ አዘዋዋሪው አልቤርቶ ዩሴፍ ለፖሊስ በሰጠው 100 ሰዓት የፈጀ ቃል ወንጀሉን ዘክዝኮታል፡፡ የፔትሮብራስ ዳይሬክተርም የመተባበር ስምምነት ተፈራርመው ቃል ሰጥተዋል፡፡ በርካታ የፔትሮብራስ ኩባንያ ኃላፊዎች፣ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ሥራ አስኪያጆች፣ የመንግሥት ሹማምንት፣ እና የመንግሥት ደጋፊ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት የተያዙ ሲሆን እነሱም ከፖሊስ ጋር የመተባበር ስምምነት በመፈራረም ወንጀሉን እያወጡ ይገኛሉ፡፡ እ.ኤ.አ. በ1995 በወጣው የብራሊዝ የወንጀል ሕግ እና እ.ኤ.አ. በ2013 በወጣው የተደራጀ ወንጀል ሕግ 12.850 መሠረት ከተጠርጣሪዎቹ ጋር የመተባበር ስምምነት ባይደረግ ኖሮ ወንጀል ምርመራው ተድበስብሶ ይቀር እንደነበር የብራሊዝ ዐቃቤ ሕጐች ይናገራሉ፡፡

አንዳንድ የብራሊዝ የሕግ ባለሙያዎች የመተባበር ስምምነት ስለመፈራረም መብት ዝርዝር ሕግ ካልወጣ የወደዱትን ብቻ መጥቀሚያ ሊሆን ይችላል የሚል ሥጋት አላቸው፡፡ እንዲሁም አንዱ ወንጀለኛ ሌሎችን በማጋለጥ ከወንጀሉ ሊታጠብ አይገባም የሚሉትም አይጠፉም፡፡ ነገር ግን የመተባበር ስምምነት የወንጀል ሠንሠለትን ሰርስሮ ለማውጣት እንደሚጠቅም ግልጽ ነው፡፡ እንዲሁም የተመዘበረ የሕዝብ ሀብትን ለማስመለስ ውጤታማ ነው፡፡ ቢያንስ የሕዝብን ሀብት ዘርፎ እፎይ ብሎ መኖርና መክበር እንደማይችል እና የትም እንደማያደርስ ትውልዱን ያስተምራል፡፡ የመተባበር ስምምነት በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥም በዝርዝር ቢካተት ሙስናን ለመዋጋት አይጠቅምም ትላላችሁ? ቸር ይግጠመን፡፡ ምንጭ የዓለም አቀፍ የጠበቆች ማኅበር መጽሔት ግሎባት ኢንሳይት ኤፕሪል/ሜይ 2015 እ.ኤ.አ.፡፡■

## ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ በሞት የተለዩ የማኅበሩ አባላት

1. አቶ ይጥና ጋሻው ኃይሌ
2. አቶ መብራህቱ ዮሐንስ
3. አቶ ሙሉ መጃ
4. አቶ ሙላት ፈለቀ
5. ሻለቃ ኤርጳሣ ደራ
6. አቶ አለማየሁ እሸቴ
7. አቶ አለባቸው ዘውዴ
8. አቶ በኩረ አሰፋ
9. አቶ ዮሐንስ ኀሩይ/ የኢትዮጵያ ጠበቆች የሕግ መጽሔት ዋና አዘጋጅ/
10. አቶ ይገዙ ዳምጤ
11. አቶ ዳኜ ረዳ
12. አቶ ውበት ተፈራ
13. ሻምበል ደበበ ካሣ
14. አቶ ዓለሙ ገበየሁ
15. አቶ ሙሉጌታ ፀጋዬ
16. አቶ ውዴ ዳመነ፣
17. አቶ ተስፋሚካኤል ተክለማርያም፣
18. አቶ ኃይለሥላሴ ገ/ መድኅን
19. አቶ ኃይሉ ነጉ
20. አቶ ይሁንፀሐይ በየነ
21. ግራዝማች አወቀ አዕምሮ
22. አ/አለቃ ፈለቀ አለማየሁ
23. ተባባሪ ፕሮፌሰር ሰላሙ በቀለ
24. ግራዝማች አማን ሁሴን
25. አቶ ንጋቱ ተስፋዬ
26. አቶ ሞላ መንግሥቱ /የሕግ ት/ቤት መምህር/
27. አቶ በጊዜው አዘዘ
28. አቶ መሐመድ ያቁት
29. አቶ ካሣዬ ተክለአረጋይ
30. አቶ መታሰቢያ ፈቃዱ
31. አቶ አሰፋ ሊበን
32. ኮ/ል መንግሥቱ ኃይለማርያም